# ይፋ አድርጎ አወጀው

የትካንቱ ምስኪን ፣ ጉስቁል ባለተስፋ
እንደ አሮጌ ቁርበት ፣ ታሽቶ የተለፋ
ጥጋብ የማይችለው ፣ እንዳይን የጠፋ
ያበላውን ወጪት ፣ እረግጦ እሚደፋ
ከበሮ የሚነርት ፣ እስኪደፍቅ አረፋ
    አሜሪካ ገብቶ ፣ በባዶ ሲያናፋ
    የሚነገር ሞልቶ ፣ የሚባል ሳይጠፋ
    ኮምዩኒታት ትግራይ ፣ የተባለው ቶፋ
    በፆመ ሁዳዴ ፣ ዛሬ ቅርሻት ተፋ ።

ሚስቱ ያነኮረችው ፣ የሚያውቀው አምባሻ
ቺዝ ነስንሰውበት ፣ ጋግረው በመጥበሻ
የፈረንጅ ቂጣ ፣ ቀርቦለት በኬሻ
ትን እስኪለው ጎርሶ ፣ በሚያሳፍር ጉርሻ
መሞቻው ሲቃረብ ፣ በስተ መጨረሻ
የሜሪካው ሃጎስ ፣ ጥርስ የሌለው ውሻ
በአቋም መግለጫ ፣ ጀመረ ንክሻ ።

እናቱ ወያኔ ፣ ተይዛ በሲቃ
መሽቶ እስከሚነጋ ፣ ምጥ ይዟት ተሳቃ
ወንበሯ ተናግቶ ፣ ተንሸራታ ወድቃ
እንደ ጃፓን ስኒ ፣ ሆና እርካሽ እቃ
ከዛሬ ነገ ሞትኩ ፣ እያለች ተጨንቃ
    የሃጎስ ስብስብ ፣ የአሜሪካን ጭቃ
    የጥርስ አልባዎቹ ፣ ተወካይ አለቃ
    ድንጋጤ ውጦት ፣ ከንቅልፉ ሲነቃ
    ቂጣ በቀደደው ፣ በዚያ አፉ ቦርቃቃ
    ይተረተር ጀመረ ፣ በጣቃ በጣቃ ።

የሻገተው ስአርዓት ፣ በስብሶ ያረጀው
እንኳንስ ለጠላት ፣ ለራሱ እማይበጀው
የነደደው እሳት ፣ ዛሬ ስለፈጀው
የሃጎስ ማንዛረጥ ፣ የድጋፍ ጀው ጀው
ወያኔን ከመሞት ፣ ካያድን ካይበጀው
ዞሮ መግቢያ ቤቱን ፣ ዛሬ እንዳያበጀው
እበት ትል መውለዱን ፣ ይፋ አድርጎ አወጀው ።

ታዛቢው

March 7, 2018